የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፶
አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No.50
Addis Ababa 23th October, 2021

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር፻፴፰/፪ሺ፲፬**
**የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ**
**የአሰራርና ሥነ-ሥርዓት ማሻሻያ ደንብ**
ገፅ..............................................፪ሺ፯፻፳፫

**Content**

**Regulation No138/2022**
**Ethical and working procedure of the Addis Ababa city cabinet Amendment regulation**
Page …………………………………….. 2723

## ደንብ ቁጥር፻፴፰/፪ሺ፲፬
## የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ
## የአሰራርና ሥነ-ሥርዓት ማሻሻያ ደንብ

የአዲስ አበባ ከተማ ከጊዜ ወደ ጊዜ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና ፖለቲካዊ ረገድ እድገት እያስመዘገበ በመሆኑና ከሚመዘገበው ለውጥ ጋር አብሮ በሚሄድ መልኩ የካቢኔ አሰራርና ሥነ-ሥርዓት ደንቡን ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁጥር ፸፬/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፱ መሰረት ይህንን ማሻሻያ ደንብ አውጥቷል፡፡

## Regulation No138/2022
## Ethical and working procedure of the Addis Ababa city cabinet Amendment regulation

**WHEREAS,** There has been the city is progressing from time to time in economic, social and political terms, and in a manner that goes along with the changes that are recorded, there is a need to improve the rules and regulations of the cabinet;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 9 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to specify the power and duties of the thereof Proclamation No. 74/2022, the Cabinet of the Addis Ababa City Government has issued this amendment Regulation.

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

**፩. <u>አጭር ርእስ</u>**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ የአሰራርና ሥነ-ሥርዓት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር ፻፴፰/፪ሺ፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"ደንብ"** ማለት የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ የአሰራርና ሥነ-ሥርዓት ደንብ ቁጥር ፻፱/፪ሺ፲፩ ነው፤

፪. በደንቡ የተተረጎሙ ቃላትና ሐረጎች በዚህ ደንብ ተፈጻሚነት አላቸው፡፡

**፫. <u>ማሻሻያ</u>**

ደንቡ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩. በደንቡ አንቀፅ ፲፬ ንዑስ አንቀፅ (፫) ውስጥ "የስብሰባ ቀን ቅዳሜ ዕለት" ከሚለው ሐረግ ቀጥሎ "ከጠዋቱ ፫ ሰዓት (ሶስት ሰዓት) ጀምሮ" የሚል ሐረግ ተጨምሯል፤

፪. በደንቡ አንቀፅ ፲፰ ንዑስ አንቀፅ (፪) ውስጥ "አጀንዳ በካቢኔ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ኃላፊ ተዘጋጅቶ" ከሚለው ሐረግ ቀጥሎ "እንደአስፈላጊነቱ" የሚል ቃል ተጨምሯል፡፡

**፬. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ ጥቅምት ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ከጥቅምት ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**1. <u>Short Title</u>**

This regulation may be cited as "Ethical and working procedure of the Addis Ababa city cabinet Amendment regulation No. 138/2022".

**2. <u>Definition</u>**

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1. **"Regulation"** means Amended regulation to provide for the ethical and working procedure of the Addis Ababa city cabinet No.109/2019;
2. The words and phrases defined in the Regulation shall also be applied in this Proclamation.

**3. <u>Amendment</u>**

The regulation is hereby amended as follows:

1. Sub-Article (3) of Article 14 of the regulation a new phrase "Starting from 9:00 AM)" is added after the phrase "Saturday shall be the ordinary meeting day of the Cabinet";
2. Sub-Article (3) of Article 18 of the regulation a new phrase "as it finds necessary" is added after the phrase "shall be prepared by the head of the Cabinet Affairs Directorate and shall be sent to the Cabinet members before three days";

**4. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall come into force as of October 23, 2022.

**Done at Addis Ababa, this October 23, 2022**

**Adanech Abiebie**

**Mayor of Addis Ababa City**